# ዛሬም እንደ ትናንቱ --- ? ያስተዛዝባል፣ ያጠያይቃል

(ግርማ በቀለ)

*የዛሬውን ጽሁፍ በጥያቄ መጀመር ፈለግሁ፡፡ "ለሰው ልጅ ከትናንቱ/ከስህተቱ ለመማር ስንት ጊዜ ይፈጅበታል፣ ለመማር ስንቴ መውደቅ ይኖርበታል?" በሚል፡፡ ይህን ጥያቄ በአገርኛ አባባል በቀላሉ መልሼ ወደ መነሻ ኃሳቤ ላምራ፡፡ ደጋግመን ወድቀናልና መልሱ "ጠዋት ስትወጣ የመታህ እንቅፋት/ድንጋይ ማታ ስትመለስ ከደገመህ ድንጋዩ አንተ ነህ፡፡" ሚለው ይሆናል፡፡ ይህን ጥያቄና ምላሽ ያነሳሁት ከሰሞኑ በተደረገና ሊደረግ በታቀደ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የታዘብኩትንና ሥጋቴን አንስቼ ለቀጣዩ ምን መደረግ አለበት ለሚለው የሚሰማኝን ለመግለጽ ነው፡፡*

1. **ትዝብት፡- በመድረክ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ፤**

ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ላይ የ "መድረክ" ጠቅላላ ጉባኤ ተሰብስቦ ምርጫ 2007 ን ገምግሞ የደረሰበትን ድምዳሜ ገልጾልን መነሳቱን አድምጠናል፡፡ መቼም አንድ ድርጅት (ፓርቲም ይሁን የፓርቲዎቸ ስብስብ) አቅም ጊዜና ሁኔታው ቢፈቅድለት በየሳምንቱ አባላቱን ሁሉ ወይም አመራሩን እያገናኘ ቢያወያይ አንዳችም የሚያስተዛዝብም ሆነ የሚያሰጋ ነገር የለውም፡፡ የአንድ ድርጅት የዕለት ተዕለት ተግባር ስለሆነ ብቻ ሳይሆን በየደረጃው ድርጅቱ የወሰዳቸውን አቋሞች ያከናወናቸውን ተግባራት ከውጤትና ከግቡ አንጻር ለአጠቃላይ አገራዊ ተልዕኮው ያበረከተውን አስተዋጽኦ ለመመልከት ስለሚረዳውና በሂደቱ ከተመዘገበው ውስንነትና ጥንካሬ ባለው መልካም አጋጣሚና አስጊ ሁኔታ ውስጥ ለቀጣዩ ወሳኝ ትግል ግልጽ/የጠራ ኃሳብ ላይ የቆመ የትግል ስትራቴጂና ዓላማ ለመቅረጽ፣ የማስፈጸሚያ ስርዓት ለመዘርጋት እንዲያስችል ነው፡፡ከዚህ አንጻር ከመድረክ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠበቅ የነበረው ፤ ከአጠቃላይ ነባራዊና በምርጫ 2007 ሂደት የታየውንና ምርጫውን ተከትሎ እየሆነ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ በመገምገምና በማገናዘብ፡-

1ኛ/ ትናንት በመሪነት ያስፈጸመው ‹‹ለምን ደጋግመን ወደቅን›› ጥናትን በዝርዝርና ጥልቀት መርምሮ ለቀጣዩ ትግል የጠራ ኃሳብ በመቀመር ግልጽ አቅጣጫና ዓላማ ማስቀመጥ፤

2ኛ/ የግንባሩን ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ በማሻሻል በግንባሩ ውስጥ ያሉትን ፓርቲዎች ወደ ውህደት ማሸጋገር እና ሌሎችን ፓርቲዎች ወደ ግንባሩ/ውህዱ ፓርቲ የሚመጡበትን ስልት መቀየስ፤

3ኛ/ በነዚህ መሰረት ለቀጣዩ ትግል ውጤት ተኮር የሁለንተናዊ ለውጥ አደረጃጀት/መዋቅርና አመራር የሚፈጠርበትን ሁኔታ ማመቻቸትና…

ይህንን ስንጠብቅ ከምንም ተነስተን አልነበረም፡፡ ከጉባኤው አስቀድሞ ‹‹መድረክ በህልውናው ጭምር ለመወሰን የሚያስችል ጉባኤ ሊያካሂድ ነው›› የሚለውን መልዕክት ትናንት በገዢው ፓርቲ ላይ ሂስና ተቃውሞ በጠንካራ ቃላት ሲቀርብ እኛ ‹‹ተሳዳቢ›› አይደለንም ይሉ የነበሩ የመድረክ አመራሮች ከተለመደው በተለየ ምሬት ተቃውሞ ሲያሰሙ ስላስተዋልን፤ከምርጫው በፊት በዚህ ምርጫ ካለፈው ምርጫ የተሻለ ውጤት ካላስመዘገብን ( ይህ ማነጻጸሪያ በራሱ ችግር ቢኖረውም) ከእንግዲህ የትግሉ አመራርነት ‹‹ይበቃናል›› ዓይነት የመረረ ኃሳብ በመስማታችንና በምርጫው ቅስቀሳ ወቅት ህዝቡ በራሱ ተነሳሽነት ያሳየውን ድጋፍና ያስተላለፈውን ‹‹ተባብራችሁ ምሩን›› ጥያቄ ፣በየአባል ፓርቲዎች የነቃ ተሳትፎ እያደረጉ ካሉት ወጣቶች፣ እና መድረክ ገዢው ፓርቲ ከምርጫ በኋላ ወሰደብን በሚለው የበቀል እርምጃ ደጋግሞ ካሰማው ጩሄት ጋር አገናዝበን በመመዘን ነበር፡፡

ይሁን እንጂ የጉባኤውን ውጤት ስንሰማ እንደተነገረውም እንደተጠበቀውም ሳይሆን በ‹‹ሥራ የፈታ መነኩሴ ቆቡን ቀዶ ይሰፋል›› ምሳሌያዊ አነጋገር የሚገለጽ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ የጉባኤው ተልዕኮና ውጤት ከተጠበቀው ጋር ሲተያይ ‹‹ፍዬል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ›› አድርጎታል፡፡ ማለትም-

መድረክ በዚህ ስለቀጣዩ ትግል ከማንም የሚሰማ ጠፍቶ በጉጉት በሚጠብቅበትና ህዝቡን አስተባብሮ ለሁለንተናዊ ለውጥ የሚመራ የትግል ማዕከል በእጅጉ በሚፈለግበት ሰዓት ጉባኤ ሲጠራ ይህንን ክፍተትና ውስንነት የሚሞላ እንዲሆን ከላይ በገለጽናቸው ተነስቶ ይቅርና በበጎ ምኞትና ቅን ፍላጎትም ቢሆን በማንም ላይ የሚፈረድበት አይሆንም፡፡ ይህ የሆነውም ህዝቡ የምርጫን ነገር በተለይም ከምርጫ 2007 ሂደትና ውጤት አንጻር ገምግሞ ጨርሶ የምርጫን ነገር ‹‹የውሾን ስም ያነሳ….›› ብሎ ደምድሞ በተነሳበትና በቀጣይ ምንና እንዴት፣ በማን እየተመራን ለምን ውጤት? የሚሉ ጥያቄዎችን አንስቶ መልስ በሚጠብቅበት ሰዓት ነው፡፡ ይህንን ከመድረክ ጉባኤ ከወጣው የአቋም መግለጫ አንጻር በሚመለከት ነው ትዝብታችን ፡፡

በዚህ ወሳኝ ወቅት መድረክ ትናንት የነገረንን ‹‹ ምርጫው ነጻ፣ፍትሃዊ፣ …. አይደለምና አንቀበለውም፣ (ከዚህ በፊት ከ33ቱ፣ ከዚም በኋላ በሂደቱ በወላይታ ዞን ከ8 ፓርቲዎች ጋር ያቀረበው ጥያቄዎች ሳይመለሱ ወደ ምርጫ ለምን ገባ ? የሚለውን ሳናነሳ)፣ ፕ/ት ኦባማ ምርጫውን ዲሞክራሲያዊ ማለታቸው አግባብ አይደለም፤ … ‹‹ነጻና ገለልተኛ›› አጣሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ ይጣራ…፣…››፣ ብሎ፣ በየጉባኤውና በየጊዜው ስለሚነሳው የውህደት ጥያቄም በገደምዳሜ ነካክቶ አልፎታል፡፡ በእውነቱ እነዚህ ሰዎች ዛሬም እዚያው ናቸው ወይስ ህወኃት/ኢህአዴግ ጽፎ የሰጣቸውን ነው ያነበቡልን ወይስ …. ? ብለን እንድንጠይቅ የሚያስገድድ ነው፡፡ ሌላው ቀርቶ ከዚህ ሥርዓት ጋር 24 ዓመት የዘለቀ፣ በተደጋጋሚ ምርጫዎች የተሳተፉ ፓርቲዎችን ያቀፈ፣ በተለይ ደግሞ በምርጫ 2007 ሂደት ያለፈና ውጤቱን የተመለከተ፣ ከምርጫው ውጤት በኋላ በዕጩዎቹ፣ በታዛቢዎቹ፣ በአባላትና ደጋፊዎቹ በተፈጸመው የበቀል እርምጃ ስለደረሰው ግድያ፣እስራት፣ማፈናቀል … በየጊዜው ‹‹መርዶ›› የሚነግረን አመራር ተነስቶ ስለ ‹‹ነጻና ገለልተኛ ›› አጣሪ ኮሚሽን/ተቋም መመስረት ሲጠይቅ የጤና ነው ትሉታላችሁ? ኢትዮጵያዊ ‹‹ጨዋነት›› ይዞን ካልሆነ ከዚህ (ከጤናው) ባለፈ ብንጠረጥርስ ይፈረድብናል?

ህዝብ ይጠብቅ የነበረው ውጤቱን አንቀበልም ብለዋልና -- ‹‹ ካልተቀበሉ ምን ለማድረግ አስበዋል ? እንዴትስ ይመሩናል? ›› ወደቤት አንገባም ብለውናልና ‹‹በቀጣይ ምን ዝግጅት አድረገው ሊነግሩን ነው?››… ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ ሆኖ ባለበት ፖለቲካውን ቅንጣት ወደፊት የማይገፋ ወይም ስለመግፋት ምልክት የማያሳይ የ‹‹አንተኛም›› ቀረርቶ ከንቱ ድካም ነው፡፡ በገደምዳሜ ስለሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ የተነሳው ያልተፈለገ ‹‹ ማስተዛዘኛ›› በቦታው አይደለም፤ ስለሙስሊሙ ኮሚቴ ከተነሳ መባል የነበረበት ስለህዝባዊ ትግል አመራር ከ‹‹ድምጻችን ይሰማ›› ተምረን ለትግሉ ህዝባዊ መሰረት አበጅተን በቀጣይነት ተከታታይ ጥያቄኣችንና ተቃውሞኣችንን ከዳር እስከዳር ህዝቡን በማንቀሳቀስ እንመራለን የሚልና ለዚህ ተፈጻሚነት ለሁሉም የለውጥ ኃይሎች (የፖለቲካ፣ ሲቪክ፣ የኃይማኖት፣ የማኅበረሰብ … ወዘተ አደረጃጀቶች) የነጻነት ትግል ትብብር ጥሪ ነበር፡፡ ከዚህ ውጪ የሆነውና ሊሆን የተዘጋጃችሁት ‹‹እየተቃወሙ ለመኖር›› የሚደረግና እየተቃወሙ መኖር ‹‹ልዩ ጥቅም›› የሚያስገኝ ዓይነት ትዝብት ላይ ይጥላልና ለህዝብ ትዝብት ከምንዳረግ(ያውም ያልተዳረግን ከሆነ) ቆም ብለን የግንባሩን አቋም፣አካሄድ፣ አመራር፣… እንፈትሽ፡፡

በዚህ መሰረት መድረክ ከ‹‹አዛውንቶች የትዝታ ክበብነት›› ወደ ‹‹የነጻነት ትግል ማዕከልነት›› መቀየር፣ ፓርቲን ከመሪው እኩል እንዲታይ የሚያደርገውንና አመራሩንም እንደ ኀበዝ አለቃ የሚያስቀጥረውን ‹‹አይነኬውን የጽዋ ማኅበር መሰል የዙርና በአንድ ሰው ላይ የተማከለ አመራር›› በ ‹‹ውጤት ተኮር የሁለንተናዊ ለውጥ ብቃት ያለው›› (የጋራ/የቡድን አመራር ስርዓት›› መለወጥንም ከግምት በማስገባት) መተካት አለበት፤ ግንባሩም ዛሬ ዛሬ የእድር ሚናም ከ‹‹መርዶ ነጋሪነት›› ዘሏልና ወደ ‹‹ትግል

መድረክነት›› ፣ በራስ ቃላት ‹‹ከመታበይ›› ወደ ‹‹ተግባር ››ይሸጋገር ብለን በግልጽ ለመነጋገር የሚያስደፍር ደረጃ ላይ ደርሰናልና ….. የህዝብ መሪ ነን ለማለት ከህዝብ አርቆ መመልከትና ቀድሞ መገኘትን ቢጠይቅም ካልተቻላችሁ ቢያንስ ቢያንስ ከህዝብ እኩል ለማየትና ከጎን ለመራመድ ወደ ህዝቡ ወርዳችሁ ለማድመጥ ሞክሩ፣… ህዝብ እየጎተታችሁ ተመልሳችሁ ልትመሩት አትችሉምና …. ፣ ትዝብቴን ቋጨሁ፡፡ በቀጣዩ ክፍል ስለሚጠበቀው የሰማያዊ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ ያለኝን ሥጋት ይዤ እመጣለሁ፤ቸር እንሰንብት//05/12/07

<u>ዛሬም እንደ ትናንቱ--- የቃላት ጨዋታ? ያስተዛዝባል፣ ያጠያይቃል//</u>

**ክፍል ሁለት፤ <u>ሥጋት፡</u>- በሚጠበቀው ‹‹ የሰማያዊ ጠቅላላ ጉባኤ ››**

የቱንም ጉዳይ በተለይም ሥጋትን በቀና እና አዎንታዊ ጎኑ መጀመር በስልጡን ዓለም ለጤናማ ግንኙነት እንደ መተዳደሪያ ደንብ የሚወሰድ ነውና እኔም ሥጋቴን በዚህ መልክ ልጀምር ወደድኩ፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ ከዚህ ቀደም በኢትዮምህዳር ጋዜጣ ለወጣት ብርሃኑ ተክለያሬድ ‹‹ <u>ሆድን በጎመን ቢደልሉት …›› ማብራሪያ ወይስ ማደናገሪያ ?</u> ›› በሚል ርዕስ ስለ ሰማያዊ ወጣቶች የጻፍኩትን እዚህ ላይ ማስታወስ አለብኝ፡፡ ይህም….. ‹‹ስለሆነም በአሁኑ ጊዜ በተቃውሞ ጎራው ባሉ ዲሞክራቲክ ኃይሎች መካከል ያለው የዓላማ ልዩነት ለመሰባሰብ ከሚያበቃቸው ተመሳሳይነት ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል ያለመሆኑንና በጋራ አብሮ ለመሥራት የሚያስማሙ ጉዳዮችን ለይቶ ለማውጣት ቅንነቱና የዓላማ ጽናቱ ካለ ብዙ አስቸጋሪ አይደለም ብዬ አምናለሁ፡፡ ይህን ለመረዳት የሰማያዊ ፓርቲ አመራርና አባላት ካለፈውና ካረጀው አስተሳሰብ ባሻገር ለማየትና በሕብረት መሥራት ላይ የያዙትን ጊዜያዊም ሆነ ዘላቂ አቋም እንደሚመረምሩትና እንደሚከልሱት በዚህም ከላይ እንዳልኩት ማንም የኅብረተሰቡን ፖለቲካዊ ንቃት፣ማኅበራዊ ዕድገትና ጊዜን ወደ ኋላ ሊመልሰው እንደማይችልና <u>ማንም ወደደ ጠላ መጪው ጊዜ የሚጠይቀው ትግልና የአመራር ኃላፊነት በወጣቱ ላይ የሚያርፍ</u> ፣በውጤቱም ከማንም በላይ ተጠቃሚም ሆነ ተጎጂ ወጣቱ መሆኑን ተረድተው የዲሞክራቲክ ኃይሎችን የጋራ ትግል የማስተባበር (ቢቻል የማዋሃድ ባይቻል የማቀናጀት) ኃላፊነት እንደሚቀበሉ ወይም የጥረቱ አካል እንደሚሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡ የአብሮ መስራቱ ችግር የቱንም ያህል ዓይነትና መጠን ያለው ይሁን፣ ይህንንም የትግሉ አካል አድርጎ በመቀበል ወደ የጋራ ትግል መድረክ ይመለሳሉ በሚል <u>በተስፋ እጠባበቃለሁ</u>፡፡ <u>በምንም መንገድ ተስፋ አልቆርጥም</u>፤ የኢትዮጵያ ልጆች ከስህተታቸው ተምረው ዛሬም እንደትናንቱ በአንድነት ቆመው ትግላቸውን ለማስተባበርና ለማቀናጀት ዕውቀቱና እውነቱ እንደማይጠፋቸውና ዳግመ-ትንሳኤዋን እውን እንደሚያደርጉ ለአፍታም አልጠራጠርም፡፡ ጥያቄው የጊዜ ጉዳይ ነውና ዛሬ ላይ በዲሞክራቲክ ኃይሎች ጎራ ያለው <u>የወጣት ኃይል</u> ይህን ለመወጣት ጊዜው አሁን መሆኑን ተረድቶ ትግሉን በማስተባበር ከገባንበት አዘቅት ያወጣናል፣የሥቃይ ዘመናችንን ያሳጥራል፡፡›› ይላል፡፡ ተስፋ እንዳደረግሁትም ሰማያዊ ኃሳቡን ቀይሮ ወደ አብሮ መሥራት መጥቶ በ9ኙ ትብብር የሰራበት ሁኔታ ነበር፡፡ ዛሬም ይህን ተስፋ ለማምከን ካለኝ ምክንያት ይዞ ለመቆየት ያለኝ ምክንያት ያመዝናልና አሁንም ተስፋ አልቆርጥም፡፡ በተጨማሪም በዚህ ዘመን በአብዛኛዎቹ ዘንድ ተፈልጎ የማይገኘውን አገር ወዳድነት፣ የዓላማ ጽናት፣ቆራጥነት፣ … ላየሁባቸው የሰማያዊ ወጣቶች በተደጋጋሚ ባገኘሁት አጋጣሚ ሁሉ የገለጽኩት አድናቆት ዛሬም ከእኔው ጋር መሆኑን አስታውሼ ማለፍ እወዳለሁ፡፡

በመቀጠል ባለፈው ትዝብታችን የገለጽንበት የመድረክ ጉባኤ ለሰማያዊ መማሪያ ይሆናል ብለን እንጠብቃለን፡፡ ህዝብ ከሰማያዊም ከመድረክ የተለየ አይጠብቅም፤ ልዩነቱ መድረክ ለተባበረ ትግል ጥንስስ የተጣለበት የፓርቲዎች ግንባር መሆኑ ነው፡፡ ሰማያዊም ከ ‹‹አፈንጋጭነት›› ተመልሶ እንደ መድረክ በግንባር ባይሆንም በ‹‹ትብብር›› ከሌሎች ጋር የጀመረው ግንኙነት ለቀጣዩ የተባበረ ትግል ጥንስስ ሊሆነው ይችላል፤ የሚፈለገው የፖለቲካ ቁርጠኝነት ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ በ‹‹ታላቅነት በሽታ›› ካልታወረ ብዙ አይቸገርም ብዬ አስባለሁ፤ ሰማያዊ በ14ቱ ጥናት ላይ እንደተመለከተው ‹‹‹‹ ኢህአዴግን ጨምሮ-ላለንበት ተጨባጭ ሁኔታ የሚመጥን ዘላቂ መፍትሄ የሚሰጥና የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት የሚችል አንድም ፓርቲ የለም፣….›› የሚለውን ተቀብሎ ከዚህ በፊት ‹‹ማን አለና፣ ከማን እንተባበር›› ካለው ኃሳብ ተመልሶ በትብብር ለመስራት የወሰደውን አቋምና ለዚህም በማዕከልነት የወሰደውን የአመራር ሚና ይደግመዋል የሚል አዎንታዊ ታሳቢ እንውሰድ፡፡ በዚህ ታሳቢ ዛሬም በሰማያዊ ወጣቶች ላይ ተመሳሳይ ተስፋ አለኝ፡፡ አሁንም የአብሮ መስራቱን መስመር ከማጠናከር ሌላ የተናጠል

ሩጫ የትም እንደማያደርስ ይረዳሉ፣ በመሆኑም ሰማያዊ ለቀጣዩ ትግል የማዕከል ሚና ከሚጫወቱ አንዱና ቀዳሚው ይሆናል የሚል ተስፋ ሰንቀን እንነሳ፡፡

ይህን እንደመንደርደሪያ ካነሳን በኋላ ወደ ተነሳንበት የሥጋት ኃሳብ እንግባ፡፡ የሥጋቱ መነሻ ምናባዊ አይደለም ካለፍንበት - ነባራዊ ሁኔታ ባለን መረጃና ከተገነዘብነው ተጨባጭ እውነታ የመነጨ ነው፡፡

ምንም መረጃ ይኑረን፣ ጽሁፋችንም ሥጋት መሆኑንና በመረጃ ያገኘነውም ሊስተካከል የመቻሉን ዕድል ከግንዛቤ አስገብተን መጪው የሰማያዊ ፓርቲ ጠቅላላ ጉባኤ (ፓርቲው የራሱን አጀንዳዎች መቅረጹና በምርጫ 2007 ግምገማ ብዙ መድከም አይኖርበትም የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ ማለት ነው) ለመጪው የተባበረና የተቀናጀ አሳታፊ አገራዊ የጋራ ትግል ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል የምንላቸውን ጉዳዮች በጥቅል እንመልከት፡፡

1ኛ/ **ከሌሎች ጋር በጋራ የመስራት ተሞክሮ ግምገማ** ፡- ከዚህ በፊት በ14ቱ የተደረገውንና ያጸደቀውን ጥናትና የፈረመውን ሰነድ በማገናዘብ ‹‹በ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር›› በማዕከልነት ሲያስተባብር የነበረው የጋራ ትግል ለሰማያዊም ሆነ ለቀጣዩ ትግል ምን አስተዋጽኦ አበርክቷል? የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር ይዞ የተነሳውን ዓላማ ምን ያህል ተግባራዊ አድርጓል ? ከሌሎች ጋር የተጀመሩ ግንኙነቶች የት ደርሰዋል ?

2ኛ/ **ቀጣዩን የትግል አጀንዳ በግልጽ ማስቀመጥ** ፡- ሰማያዊ በቀጣይ የድርጅቱን ፕሮግራምና ዓላማ የሚያስፈጽምበትን መንግስት ለመመስረት በተናጠል ይታገላል ወይስ በብሄራዊ ዕርቅ ለሚያልፍ የሽግግር መንግስት ምስረታ ከሌሎች ጋር በትብብር ይሰራል? ከሌሎች ጋር በተለያዩ የግንኙነት ደረጃ (ቅንጅት/ግንባር/ውህደት) ለመስራት ከወሰነ በፕሮግራሙና መተዳደሪያ ደንቡ ማሻሻያ/ክለሳ ማድረግ ይኖርበታል/አይኖርበትም ? ዲሞክራቲክ የለውጥ ኃይሎችን በማስተባበር ረገድ ማዕከላዊ ሚና እንዲኖረው ምን ማድረግ ይኖርበታል?

በእኔ እምነት በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ጊዜ ወስዶ በጥልቀት ተወያይቶ የማያሻማ አቋም ይዞ ካልወጣ የጉባኤው ተልዕኮ የምርጫ ቦርድን ፎርማሊቲ ከማሟላትና የድርጅቱን ህልውና ማስከበሪያ ከመሆን ያለፈ ፋይዳ እምብዛም አይታየኝም፡፡ ይህ ካልሆነና ወደ ውስጡ መመልከት ካልቻለ እየፎከረ፣ በማኅበራዊ ሚዲያ ‹‹ዕለታዊ መርዶ›› እየነገረን በተግባር በአዲስ-አበባ እንዲገደብ ይገደዳል፡፡ ሲያልፍም በህወኃት/ኢህአዴግ ረጅም እጅ በአንድነትና መኢአድ ላይ ላረፈው በትር ይዳረጋል፡፡ የመጥፎ ምኞት መግለጫ አይደለም፣ ትናንት ስንናገር በ‹‹ታላቅነት በሽታ››/ግብዝነት በሌሎች ላይ የደረሰውን ስለምናውቅ ‹‹ ማን ይናገር የነበረ፣ ማን ያርዳ የቀበረ›› እንዲሉ ባለፈው በቅርበት በተደጋጋሚ በተግባር ከተመለከትነው ያደረብን ስጋት ነው፡፡ ይህ ስጋት በሰማያዊ ህልውና እና በሰማያዊ የተሰባሰቡት የማደንቃቸው ወጣቶች እንደ አንድነትና መኢአድ ትንታግ ወጣቶች ተበትነው እንዳይቀሩ ከሚል ብቻ አይደለም፤ ከዚህ ባለፈ እነዚህ ወጣቶች በሰማያዊ ከሌሎች ጋር በኅብረት በጋራ አገራዊ አጀንዳ ላይ ቢሰሩ የተበተነውን የለውጥ ኃይል በማሰባሰብ ቌምር ሊያበረክቱት የሚችሉት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ‹‹በፓርቲ ጥቅም ማስከበር›› ሥም ባክኖ እንዳይቀር ( በአንድ ፓርቲ የተናጠል ትግል ለውጥ አይመጣም፣ ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ከፓርቲ ጥቅም፣ ፕሮግራም፣ ርዕዮተ ዓለም … አልፎ የአገር ህልውና ጥያቄ ሆኗል በሚለው የጋራ መግባባት መሰረት) የሚለውን አገራዊ ጉዳት ያገናዘበ ስጋት ነው፡፡ ይህ ስጋት እውን እንዳይሆን ምኞቴ ብቻ ሳይሆን በሰማያዊ ወጣቶች ላይ ያለኝ ተስፋም ያግዘኛል፡፡

**እንደ-ማጠቃለያ፡- ለሁሉም ዲሞክራቲክ የለውጥ ኃይሎች-**

ዛሬ እውነት እውነቱን መነጋገር ከምንገደድበት ደረጃ ደርሰናል፡፡ እስከዛሬ ‹‹ትግሉን ይጎዳል›› እያልን ሃቁን መደበቃችን ማብቃት አለበት እላለሁ፡፡ እኛ በተደጋጋሚ በአደባባይ ለህዝብ ቃል እየገባን ባልነው ያለመገኘታችን ክሽፈትን የሚሸከም የህዝብ ትከሻ መዳከሙንና ለዚህ ጀንበር ማዘቅዘቋን ልንረዳ ይገባል፡፡ በህዝብ ስም የሚፈጸመው የትም የማያደርስ ሰሞነኛ ሆይ-ሆይታ ግን ‹‹ በጅብ ባልነታችን›› ከፍተኛ ዋጋ እያስከፈለን ያለው የተናጠልና መጠላለፍ አካሄድ መስተካከል አለበት፡፡ የጠላቴ- ጠላት ጊዜያዊ ወዳጅነት/ግንኙነት በነጠረ የጋራ ትግል ኃሳብና መተክል/መርህ ዘላቂ ግንኙነት መተካት ግድ ከሚልበት ደረጃ መድረሳችን ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በመቻቻል ስም መሸካከሙ፣ ለ‹‹ዋናው ዓላማ››

በሚል ድክመታችንን መሸፋፈኑ ማክተም አለበት፡፡ ይህንን ስንል ትኩረታችን በግለሰቦች ማንነትና የግል ስብዕና ላይ አድርገን አይደለም፣ የሰላማዊ ዲሞክራቲክ የለውጥ ኃይሎች የእስከዛሬ መስዋዕትነትና አስተዋጽኦ መካድም አይደለም፡፡ ለክሽፈት የዳረገንን ድርጅቶቹ/ፓርቲዎቹ ያራመዱትን አቋም፣ የአደረጃጀት፣ የአመራር፣የአሰራርና ያከናወኑትን ተግባር ውስንነት ማለታችን እንጂ፡፡ በዚህ ወቅት ይህን እንድንል ያስገደደን ደግሞ ስህተቶች ሲደጋገሙና ለውድቀት ሲዳርጉን ማየታችን ብቻም ሳይሆን ካለፈው ‹‹ተማርን›› ብለን ከተማማልን በኋላም ‹‹ድመት መንኩሳ ዐመሏን አትረሳ›› እንዲሉ ሆኖብን ተመሳሳይ ስህተቶች እየፈጸምን በተለመደው የክሽፈት መንገድ ለመቀጠል እየተንደረደርን መሆኑን በማስተዋላችን ማንንም ከማንም ሳንለይ ይብቃንና የጋራ አገር አድን መፍትሄ ለመፈለግ እንነሳ የሚል ጥሪ ለማስተላለፍ ነው፡፡

በመሆኑም - ከዚህ ቀደም ‹‹እንጋፋው ያልተመለሰ የህዝብ ጥያቄ›› በሚል በፌስ ቡክ ገጼ ላይ ባሰፈርኩት ጽሁፍ መጨረሻ ላይ ያልኩትን ዛሬም እደግመዋለሁ፡፡ ‹‹… በርዕዮተ ዓለም፣ በፕሮግራም ምርጥ ነኝ፣ በድርጅታዊ ጥንካሬ አንደኛ ነኝ….ስለሆነም በተናጠል ትግል፣ መንግስት ለመመስረት እንታገላለን ፣ ወይም ከዚህ ወይም ከዚያ ፓርቲ በዚህና በዚያ እለያለሁ በማለት ተመራጭነታችሁን ለማሳየት ስትራቴጂ የምትቀይሱ ጓዶችን መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ፡፡ ለእኔ ግን መንገዴ እንደ ዜጋም እንደ ፓርቲ አመራርም ወደ ዘላቂ መፍትሄው መዳረሻው አንድና አንድ ብቻ ነው፤ በብሄራዊ ዕርቅ አልፎ የሚመሰረት አካታች /ገዢውን ፓርቲ ጭምር/ የሚያሳትፍ የሽግግር መንግስት ›› ፡፡ ይህ ኃሳብ የግሌ ሳይሆን በ14ቱ ፓርቲዎች ጥናት ላይ መግባባት የተደረሰበትን ለማጠናከር መሆኑ ሊጠቀስ ይገባል፡፡

የጋራ አጀንዳችን ግልጽ መሆን አለበት፤ይህም ይህን አምባገነናዊ ስርዓት በተባበረና በተቀናጀ ህዝባዊ ትግል አስገድደን ወደ ድርድር በማምጣት ወይም በመገርሰስ፣ ግን ‹‹በመቃብሬ ላይ የሚለውን ቀልብሰን›› ሳናስደነብረው፣ ሳንገለውና ሳናገለው በብሄራዊ-ዕርቅ አልፈን ሁሉን አቀፍ የሽግግር ስርዓት መመስረት ነው፡፡ ይህ የጋራ አጀንዳችን ሲሆን ለአገራችን ውስብስብ ችግሮች ዘላቂ መፍትሄ በጋራ ማበጀት ጊዜ የማይሰጠው የሁላችንም ( ከዲሞክራሲያዊ የለውጥ ኃይሎች አልፎ በገዢው ፓርቲ ውስጥ ያሉትን የለውጥ ኃይሎች ጨምሮ-- በየጊዜው የተለየ ኃሳብ በማንሳታቸው በከሃዲነት የሚታሰሩትን የሚታፈኑትን፣ የሚሰደዱትን ስናስብ እንዲሁም ስለ ውስጥ ሽኩቻው ከሚደርሰን መረጃ የመኖራቸው እውነታ አያጠያይቅም) ተግባር መሆኑ ግልጽ ይሆናል፡፡

ስለዚህ በዝነውን ጉዳይ ትዝብትና ስጋት ደርድረን መደምደሙ እርባና የለውምና የጋራ አጀንዳችንን ማስፈጸሚያ የቀጣዩ የተባበረና የተቀናጀ የነጻነት ትግል የመፍትሄ ኃሳብ ፈንጥቀን እንድንለያይ ግድ ይላል፡፡ በእኔ እምነት መፍትሄው የእስከዛሬውን አካሄዳችንን መርምረን የተለመደውን አደረጃጀት፣ አመራርና አሰራር አስተካክለን የድርጅቱ ጥቅም፣ የብሄረሰቤ ጥያቄ፣ የ… በሚል በእናቴ መቀነት ጠለፈኝ የማይደናቀፍ የተቃዋሚዎች የተባበረ ጠንካራ ሰላማዊ የነጻነት ትግል ኃይል ለመፍጠር---- የሚከተሉትን እንመርምር፡፡

1.**አደረጃጀት**-- ከተለመደው የይስሙላ ወይም በማዕከልና በፖለቲካ ፓርቲዎች ከተገደበ የአደረጃጀት መዋቅር ህዝባዊ መሰረት (ከፖለቲካ ድርጅቶች ውጪ ያሉ ማኅበራዊና የሙያ …አደረጃጀቶችን ታሳቢ ያደረገ)፣ አሳታፊ፣ ቀጣይነት ላለው ትግል የሚውል - ለዚህም የድርጅቶች በነጠረ ኃሳብ ላይ በጋራ አገራዊ ዓላማ ዙሪያ በኅብረት በመቆም አቅማቸውን ማሰባሰብና ማስተባበር የሚችል አደረጃጀት/ መዋቅር መዘርጋት፤

2.**አመራር**--- ከተለመደው ለፓርቲ መሪዎች ‹‹የኅበዝ አለቃ›› ቦታ ከሚሰጠው፣የግል ስብዕና ግንባታ ዕድል ከሚከፍተውና የአይተኬነት ስሜት ከሚፈጥረው፣ በአንዳንዶች የተቃውሞ ፖለቲካ ኅራውን እንቅስቃሴ ከግለሰብ መሪዎች ጋር አስተሳስረው ለሚያስቡ (የግለሰቦች የአመራር ብቃት የሚያመጣውን ልዩነትና ልምድና ባህላችን ከግምት ሳይወጣ)፣ አልፈውም የኢትዮጵያ ህዝብ ለግለሰብ እንጂ ለድርጅት/ፓርቲ አመራር አልበቃም እስከሚል አስተሳሰብ የደረሱበትን የሚሽር የአመራር ሥርዓት መተግበር (ከግለሰብ አመራር ወደ ጋራ/ቡድን አመራር መሸጋገርን ከግምት ማግባት)፤

3.**አሰራር**--- ከተለመደውና በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ሥም በማዕከል ከታሰረው የአሰራር ሥርዓት ተላቆ ለሁሉም መዋቅር ግልጽና የማያሻማ ሥልጣን፣ተግባርና ተጠያቂነት የሚጥል፣የየመዋቅሩን

የአሰራር ስነምግባርና ዲስፕሊን ያካተተ፣ በሁሉም መዋቅርና አባላት ተቀባይነትና ተፈጻሚነት ያለው መርህን የሚከተል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤

ለዚህም በ14 ፓርቲዎች የተደረገው ‹‹ ለምን ደጋግመን ወደቅን›› ጥናት እና የ9ኙ ፓርቲዎች ትብብር ስምምነት ሰነድ ለቀጣይ ግንኙነት ለውይይት መነሻ ሊውል ይችላል፡፡ ( በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተካተቱት ኃሳቦችም ከነዚህ ሰነዶች የመነጩ ናቸው፡፡)

በመጨረሻም በቅርቡ ከዚሁ ማኅበራዊ ሚዲያ ባገኘኋቸው የብራዚላዊው ደራሲ ፓውሎ ኮ'ሊሆ ሁለት ምርጥ አባባሎች ላብቃ፡፡ ‹‹ ስትሸነፍ አይደለም የተሸነፍከው፤ በቃኝ ብለህ ስታቆም እንጂ ! ›› እና ‹‹የሕይወት ሚስጥሩ ሰባት ጊዜ ወድቆ፣ ስምንት ጊዜ መነሳት ነው፡፡›› ይላሉ፡፡ እነዚህ ለውድቀታችን መጽናኛ እንዳይሆኑ በማስተዋል ፣ ግን ደግመን ለመነሳታት ስንቅ አድርገን- ምንም ደጋግመን ብንወድቅ ለመነሳት ፍላጎቱ፣ ቁርጠኝነቱና ፍቃደኝነቱ በእኛ ውስጥ ካለ ረፈደ እንጂ አልመሸም፤ ራሳችን ፈቅደን ካልጋበዝነው አንሸነፍምና ለስምንተኛው መነሳት በጋራ እንስራ፡፡ በስደት ካለ የቀድሞ ወዳጄ ጋር በስልክ ስንጨዋወት ያለኝም ይህንን ያጠናክረዋል ‹‹ወደ ገሃነምም ለመድረስ ቢሆን ጉዞውን (የጀመርከውን) አታቋርጥ//››

የየቱም ፓርቲ ሆነ የፓርቲ ስብስብ ከዚህ ሌላ እንዘጭ እንዘጭ ለገዢው ፖርቲ የመድብለ ፓርቲ ስርኣት ማሳመኛና ሽፋን መስጠት ሆኖ ከማገልገል ሌላ ቁምነገር አይኖረውም፤ የምርጫ ቦርድ ሰርቲፊኬትም ሆነ የፓርቲ ኅልውና ብሎ ነገር ለሠላማዊ የነጻነት ትግሉ ካልዋለ ለአምባገነን ሥርዓቱ ይሁንታ በመስጠት ሥቃያችንን ከማራዘም ውጪ ለአገርና ህዝብ የሚፈይደው የለም ፡፡ በዚሁ አበቃሁ፡፡

*09/12/07*